
# የፒያሳ ልጅ

ደራሲ - ፍቅሩ ኪዳኔ
ቅኝት - መስፍን ማሞ ተሰማ

## መነሻ




በምኖርበት ከተማ ሲድኒ ውስጥ የአማርኛ መፃህፍት አስመጪና አከፋፋይ የለም። ይህንን ችግር የሚያውቁ በሜልበርን ከተማ የሚኖሩ ወዳጆቼ ባመቻቸው ቁጥር የኢትዮጵያዊያን መናኸሪያ ወደ ሆነችው 'ፉት ስክሬይ' ወደምትባለው ቀበሌ እየዘለቁ በዚያ ከሚገኝ የመፃህፍት መደብር የአውስትራሊያን ምድር ከረገጡት አዳዲስ የአማርኛ መፃህፍት መካከል የቻሉትን ያህል ይልኩልኛል።

ከእለት የህይወት ኑሮ ሩጫ ባሻገር ከሚቀረው ጊዜ አንፃር በእጄ ገብተው ለመነበብ 'ወረፋ' ሲጠብቁ ከሰነበቱት መኻል 'የፒያሳ ልጅ'ን አነበብኩ። እና እንደደረሰኝ ማንበብ ባለመቻሌ የህሊና ቁንጥጫ ተሰማኝ። ለምን? ምክንያቱም ይህንን መፅሀፍ ማንበብ የሚችል ኢትዮጵያዊ ሁሉ ያነበው ዘንዳ የሚገባ ነው ብዬ በማመኔ። ደግሞም ይህንን እምነቴን ቀደም ብዬ ለአንባብያን ማካፈል ባለመቻሌ። በ'ፒያሳ ልጅ' ላይ ላካፍላችሁ የምፈልገው ምንድን ነው? ለምላሹ እነሆ 'የፒያሳ ልጅ' ....

## መግቢያ

የፒያሳ ልጅ በአስራ ስድስት ምእራፋት ተከፋፍሎ፣ 456 ገፆች ሲኖሩት፣ ከሃምሳ በላይ በሚሆኑት ገፆቹ "እንዴት አይናገር ይናገራል ፎቶ..." እንዲሉ፣ ማራኪና ታሪካዊ የሆኑ የፎቶግራፍ ማስረጃዎች ያካተተ ሲሆን የህትመት ዘመኑም 2009።

(እዚህ ላይ አንባቢ በእዝነ ልቡናው ቆም ብሎ 'ታዲያ ቢያንስ ሁለት አመት የሞላውን መፅሀፍ እንደ አዲስ መቃኘት ስለ ምን አስፈለገ?' ማለቱ አይቀሬ ነው።

ታሪክ እንደ ወይን ጠጅ ይመሰላል። እንዴት? ቢሉ፦ የወይን ጠጅ እድሜው በጨመረ ቁጥር ተፈላጊቱ፣ ጣእሙ እና ውድነቱ የዛኑ ያህል የሚጨምር ሲሆን፣ መልካም ታሪክም ዘመናትን ባሳለፈ ቁጥር ይበልጥ ተወዳጅ፣ ይበልጥ አስተማሪ ይበልጥ ተፈላጊና ይበልጥ ውድ እየሆነ ይሄዳልና ነው። የፒያሳ ልጅ ደግሞ የሰነቀው ታሪክ ነውና ይህንን ታሪክ ለማያውቁት መቼም ቢሆን መቼ አዲስነቱና አሳዋቂነቱ/አስተማሪነቱ በእድሜ ዘመኑ

የሚገደብ ባለመሆኑ - እንደ ወይን ጠጅ ተፈላጊነት - ቀድመው የፒያሳን ልጅ ላላወቁ ሁሉ ዛሬ 'አዲስ መፅሀፍ' ስለሚሆን፤ የሚል ይሆናል ምላሹ።)

የፒያሳ ልጅ አፃፃፉ ግለ ታሪክ (ባዮግራፊ) ይሁን እንጂ በዋናነት የታሪክ መፅሀፍም ጭምር ሆኖ ነው የሚገኘው። ለአያሌ አመታት በሀገራቸውና በውጭው አለም በጋዜጠኝነት (ከተለያዩ ሀገራዊና አለም አቀፋዊ የሙያ ሃላፊነቶቻቸው በተጨማሪ) የሰሩት አቶ ፍቅሩ ኪዳኔ በፒያሳ ልጅ መፅሀፋቸው አለአግባብ ያባከኑዋቸው ቃላት አይገኙም።

ግዙፍና ብዙ ትንታኔ የሚያሻቸውን ርእሰ ጉዳዮች ሳይቀር (ለምሳሌ ከሃምሳ በላይ የሚሆኑትን የአፍሪካ ሀገራት የፖለቲካ፤ የኢኮኖሚና የማህበራዊ ህይወት፤ የተፈጥሮ ሀብትና የአምባገነን መሪዎቻቸውን የአገዛዝ ባህል) እጥር ምጥን ብለው በሚፈነዱ አረፍተ ነገሮች እያሰሩ እያዋዛ እንደ ጅረት በሚፈስ አቀራረብ ከግማሽ ምእተ አመት በላይ ያቀፈ ታሪክ አቅርበዋል። ትርክቱ ባንደኛ መደብ ያፃፃፍ ስልት መሆኑ ደግሞ መፅሀፍ የምናነብ ሳይሆን አቶ ፍቅሩ ግዘፍ አካል ነስተው ከጎናችን በመቀመጥ ቡና በፊንጃል አብረናቸው እየጠጣን የሚያወጉን አስመስሎታል።

በአቶ ፍቅሩ ኪዳኔ ረዥም የህይወት ጉዞ ውስጥ ቆጥረን የማንዘልቃቸው የዚያ 'የደጉ ዘመን' ትውልድ ኢትዮጵያዊያንን እንተዋወቃለን። ከልጅነት እስከ እውቀት ያሳለፉትንና ያለፉበትን ታሪክ (አቶ ፍቅሩና በመፅሀፉ ላይ የተወሱት እጅግ በርካታ የጥንቶቹን ኢትዮጵያዊያንን ጨምሮ) በትውስታነት ብቻ ያቀረቡት ሳይሆን ከዛሬይቱ ኢትዮጵያ ታሪክና ትውልድ አንፃርም አቆራኝተን እንመለከት ዘንዳ ባፃፃፍ ስልታቸው አመቻችተውልናል።

ከጉለሌ የጀመረው ታሪክ የፒያሳንና የአራዳን አመሰራረትና ልጆች አስተዋውቆን በዘመናት ሂደቱ አዲስ አበባን፤ ኢትዮጵያን፤ አፍሪካንና አለምን አካሎና እንደ መስታወት እያሳየን በህይወት የሌሉትንና እንዲሁም ዛሬ አዛውንት የሆኑት የአራዳ ልጆች ለውዲቱ ኢትዮጵያ በየተሰለፉበት መስክ ያበረከቱትን ምሶሶ ተግባራት በግሩም አቀራረፅ ስሎ አቅርቦልናል።

የፒያሳ ልጅ፦ ካስተማሪነት እስከ አምባሳደርነት፤ ከሚኒስትር እስከ ጀኔራል፤ ከአቶ እስከ ፕሮፌሰር፤ ከሾፌር እስከ ፓይለት፤ ከስፖርት እስከ ህክምና ወዘተርፈ በኢትዮጵያ፤ በ አፍሪካና ባለም መድረኮች ተሰልፈው ሀገራቸውንና ህዝባቸውን በአርአያነትና በመልካም ምግባር ያስጠሩትን የዚያን ትውልድ ኢትዮጵያዊያንን ታሪክ ይዘክራል።

እርግጥ ነው በመፅሀፉ ውስጥ አልፎ፤ አልፎ በግማሽ ወይም ባንድና በሁለት ገፆች ሙሉ የስም ዝርዝሮች ብቻ ይገኛሉ። እነሂህ ዝርዝሮች በፒያሳ ልጅ ውስጥ በየምእራፉ ከተለያዩ የታሪክ ሂደቶች ጋር በቀጥታ ተቆራኝተው ከቀረቡት ሌላ በመሆናቸው ለተወሰኑ አንባቢያን የግለሰቦቹ ስሞች በጥቅሉ መቅረቡ ፋይዳው ብዙም ላይታያቸው ቢችል መፅሀፉን ከማስቀመጥ ይልቅ የስም ዝርዝሮቹን ተራምደው ወደ ታሪኩ ማለፍ የሚችሉ ሲሆን ይህም በመፅሀፉ ይዘት/መልእክት ግንዛቤያቸው ላይ የሚፈጥረው አንዳችም ጎዶሎነት አይኖርም። የስም ዝርዝሮቹ 'በአንድ ድንጋይ ሁለት ወፍ' እንደማለት ናቸው። ለሚያውቋቸው ትውስታ፤ ለማያውቋቸው ታሪክ!

*"ያገራችን ባህል መታወቂያችን፤ መመኪያችንና መኩሪያችን ነው። ወደ ውጪ የተሰደድነውንም አሰባስቦ ያኖረናል። ከንግሥተ ሳባ ዘመን አንስቶ የኦርቶዶክስና ሌሎቹን ሃይማኖቶች አክብረን፤ ዘመን አቆጣጠራችንን ሳንቀይር፤ የራሳችንን ፊደልና ቋንቋ*

*እንዲሁም እንደ ላቲን ተመሳሳይ ግዕዝ አስፋፍተን፣ የራሳችንን ልብስና በርኖስ ነድፈን፣ ልዩ ልዩ ዓይነት ምግቦች አዘጋጅተን መኖሩ ያኮራናል፣ ያስከብረናል።*

*"የስእል አሳሳላችን፣ ልዩ ልዩ ዘፈኖችና ጭፈራዎች፣ ጋሻና ጦሩ፣ ድስትና ምጣዱ፣ እንስራው፣ ስልቻውና መሶቡ መታወቂያችን ናቸው። ሁሉም ዘር ተቀላቅሎ ቤት ያፈራውን ተከፋፍሎ መኖር ፀጋ ነው። በረዥም ዘመን ነፃነቷ የምትኮራ፣ አረንጓዴ ብጫና ቀይ ሰንደቅ ዓላማ የምታውለበልብ አገራችን ኢትዮጵያ ነች። ከዓመታት በኋላ የአስተሳሰብ፣ የ አኗኗር፣ የጉርብትና፣ የማህበራዊ ኑሮ ቁርኝት ተለዋውጦ፣ ማሽክሽክ ተስፋፍቶ፣ የዘር ልዩነት ተከስቶ፣ እርስ በርስ መፋጀት፣ መገዳደል፣ መናቆር፣ መቀያየም ስር ሰዶ፣ ውቃቢ ቢርቀንም፣ ታሪካችንን ለማንኳሰስ ቢሞከርም ባህላችን ከዘራ ሆና ታራምደናለች። ... ባሁኑ ወቅት እድሜው 35 ዓመት የሆነው ሁሉ የኛን ዘመን ኢትዮጵያን ስለማያውቃት ለማመሳሰል እንዲመቸውና እንደኔ እንዳይቆጨው ቤተ ዘመዶቼ እንዲረዱትና መፅሀፍ በማንበብ ያገራችን ባህልና ታሪክ ጠባቂ እንዲሆኑ ተስፋ አደርጋለሁ።"* ይላሉ አቶ ፍቅሩ።

እነሆ ይህ ቅኝት ዓላማው የፒያሳን ልጅ ላላነበቡ ፍንጭ በመስጠት ፍላጎታቸውን ለመቀስቀስ ላነበቡትም ደግሞ ለመማማሪያ እንዲሆን ነውና በተለያዩ ንኡስ ርእሶች የተዋቀረው ቅኝት እንደሚከተለው ይነበባል።

## ያ! ዘመን!

*"አንድ ሽማግሌ ሲሞት አንድ ቤተ መፃህፍት እንደ ተቃጠለ ይቆጠራል"* ይህ ዘመናትን የተሻገረ ብሂል ነው። ይህንን ብሂል በመግቢያቸው ያሰፈሩት አቶ ፍቅሩ ዛሬ በሰባዎቹ የእድሜ ክልል ውስጥ እንደሚገኙም አክለው ገልጠዋል።

*"በወጣትነት እድሜ በዝናቸውና በጀግንነታቸው የማውቃቸውን ሰዎች ታሪካቸውን ሳልረዳ መቅረቴ ያሳዝነኛል። ይባስ ብሎ የኛም ትውልድ ቢሆን ተጨባጫ መረጃዎችን አልተወም። ... ስለዚህ ነው መፃህፍት ቤቱ ከመቃጠሉ በፊት በኛ ዘመን የወጣትነት ኑሮ እንዴት እንደነበርና ለእናት ሀገሬ ያለኝን ምኞት ለአዲሱ ትውልድ ለማሳወቅ የ'ፒያሳ ልጅ' በሚል ርእስ ይህንን መፅሀፍ ያዘጋጀሁት"* ይላሉ ደራሲው።

የአንድ አዛውንት ሞት ከቤተ መፃህፍት መቃጠል ጋር ተዛምዶ የመነሳቱን እውነታ ጥልቀትና ስፋት በትክክል የምንገነዘበው ግን 'የፒያሳ ልጅ'ን አንብበን ማሳረጊያው ላይ ስንደርስ ብቻ ነው። ከዛ በፊት ስለዚህ የዘመናት ብሂል ከመፅሀፉ ጋር አቆራኝቶ ማብራሪያ መስጠቱ ጉንጭ ማልፋት ይሆናል። ከዚህ ሌላ አቶ ፍቅሩ የሰጡት ምክንያት ደግሞ አመርቂ ነው። ለማንኛውም አዛውንቱ የአራዳ ልጅ አቶ ፍቅሩ ስለዛ ዘመን ምን ይላሉ?

*"በኛ ዘመን ማዘጋጃ ቤት የቀየሰልን ቀበሌ ስላልነበር ከአቡነ ጴጥሮስ ሀውልት አንስቶ በ አዲስ አበባ በቅድሚያ የተሰራውን አስፋልቱን ጎዳና ተከትሎ እስከ ገፈርሳ ያለውን ጉለሌ ነበር የምንለው። ... የጉለሌ ዋናው ምልክቱ ጣሊያኖች የሰሩት የራስ ደስታ ዳምጠው ሆስፒታል ሀኪም ቦራ ነበር። ...በኢትዮጵያ ውስጥ ለመጀመሪያ ጊዜ በአሳንሰር (ሊፍት) የተሳፈርን የጉለሌ ልጆች ነን።..."*

መቼም ሀኪም ቦራ የሚለውን የራስ ደስታን ሌላ መጠሪያ ስናነብ እንኳንና የዛሬው ትውልድ ሊያውቀው ቀርቶ ለሰነበትነውም ከትውስታችን ወጥቶ ነበር። ሀኪም ቦራ የስንቶችን ህይወት አድኗል? ስንቶችስ ወደዚህች አለም ሲመጡ የሀኪም ቦራን ግቢ አየር ለመጀመሪያ ጊዜ ስበው አምርረው አልቅሰውበታል?

ስለሻይና ፓስቴ (የዘመኑ ጣፋጭ ምግብ) ቤቶች ሲያወጉን ደግሞ፤ *“…በአዲስ አበባ ከታወቁት ፓስቴ ቤቶች አንደኛው መስፍን ሀረር መንገድ ይገኝ የነበረው የሸሪፍ ፓስቴ ቤት ሲሆን…ሶስተኛው ላዩ ላይ ስኳር ያለው ፍልውሃ አጠገብ ነበር።”* ይሉናል። እኔ ደግሞ ይህንን ሳነብ የሚከተለው ትዝ አለኝ።

በእኛ ዘመን (ምናልባትም አቶ ፍቅሩ አያውቁት ይሆናል) አራተኛው(?) ከባላባት (መድሃኔ አለም) ት/ቤት ጎን ይገኝ የነበረውና የአዳሜን ተማሪ አስር ሳንቲ ሙልጭ አድርጎ የጨረሰው የ’ጋርዮሽ ሳንቡሳ ቤት’ ነበር። አሁን እንኳን ይኑር አይኑር አላውቅም። የፒያሳዎቹም ‘ድል አድራጊው’ እና ‘ኬብ’ ሻይ ቤቶች ብዙ ጉደኛ ታሪክ የተሸከሙ ነበሩ፤ በተለይ በዘመነ ኢህአፓ።

እንመለስ ወደ አቶ ፍቅሩ፤

*“ጥንት ልጆች ሆነን ባገራችን ባህል መሰረት የሚከበሩትን በአሎች በሙሉ በደንብ እናከብር ነበር። ዋናው የወንዶች በአል በነሀሴ ወር የሚከበረው ቡሄ ነው። …የቡሄ ጭፈራና ዘፈኖች ‘ሆያሆዬና አሲዮ ቤሌማ’ ወግና ስርአት አላቸው። ‘ሆያሆዬ ጉዴ/ጨዋታ ነው ልማዴ’ በማለት እውነት መናገር ነው።”* የሉናል ስለዛ ዘመን የበአላት አከባበር ሲያወጉን።

ወግና ስርአትን ተከትለው፤ በባህላዊና ጥንታዊ ግጥሞች ታጅበው፤ ነፍስን በሀሴት የሚያስፈነድቁትን ቀደምት የኢትዮጵያ ባህላዊ አከባበሮችን አስመልክቶ አቶ ፍቅሩ በሰፊው አቅርበዋል። ይሁንና ዛሬ ዘመን በአብዛኛው ጣእማቸው ከመጥፋቱም ባሻገር በ አላቱን (ቡሄ፤ እንቁጣጣሽ፤ መስቀል) ወግ ማእረጋቸውን እንደጠበቁ፤ እንደ ጥንቱ እንደ ጠዋቱ በባህላዊ አለባበስና በጥንታዊ ግጥሞች አጅቦ የሚያከብራቸው ወጣት ምን ያህል እንደሆን ስናስብ በዚህ ዘመን ያለውን ትውልድ አንዳች የሆነ ባዶነት  እየጀቦነው እንደሆን በሀዘን እንረዳለን።

አኩሪና አስደናቂ የሆኑትን የባህላችንን እሴቶች ይህ ትውልድ በማወቅም ሆነ ባለማወቅ እያደበዘዛቸው ብቻም ሳይሆን እየጠፉም (ለምሳሌ ቡሄና አበባየሆሽ) ያሉ ይመስላል።

ምንም እንኳን የስልጣኔውና የቴክኒዮሎጂው እርከን ከዛን ዘመኑ የተለየ ቢሆንም ባህል ግን ባህል ነውና እንደ ዘመኑና እንደ ትውልዱ የሚቀየር መሆን አይኖርበትም። በዚህ አያያዛችን ከቀጠልን እንደ ውሃ ላይ ኩበት ማረፊያ የሌለን የምንሆንበት ጊዜ መምጣቱ አይቀርም።

የኢትዮጵያ የመጨረሻው ንጉሠ ነገሥት በሆኑት በግርማዊ ቀዳማዊ ሃይለስላሴ ዘመነ መንግስት በኢትዮጵያ ከፍትኛ የትምህርት መስፋፋት ስለመደረጉና ለምሳሌ የንግድ፤ የመምህራን ማሰልጠኛ፤ የሲቪል አቪዬሽንና የቴሌኮሙኒኬሽን ወዘተ ተቋማት ተከፍተው ግልጋሎት መስጠታቸውንና ከእኒህ ተቋማትም የተመረቁ የዛን ዘመን ትውልድ አካላት በ ኢትዮጵያ እድገት ውስጥ የተጫወቱትን ሚና አቶ ፍቅሩ በዝርዝር አቅርበዋል። ታዲያ ትውስታዎቻቸውንም አልነፈጉንም…

*“…በዚያን ዘመን በወንድና ሴት ልጆች አስተዳደግ እንጂ በትምህርት ደረጃ ልዩነት አልነበረም። በኛ ዘመን ሰአት የነበረው ተማሪ አልነበረም። የኛ ሰአት ጭንቅላታችን ውስጥ ነው። የፀሀይና የዶሮ ኩኩሉ ድጋፍ ቢኖረንም ከደወል በፊት ት/ቤት ደርሰን ተምረን ወጥተናል። ማርፈድ የጀመርነው ሰአት ገዝተን እጃችን ላይ ካሰርን በኋላ ነው”* ይላሉ።

ንጉሡ ነገሥቱ ለትምህርትና ለተማሪዎች የነበራቸውን ክብርና ልዩ ትኩረት በግሩም መንገድ ከዘረዘሩዋቸው ውስጥ ለአብነት የሚከተለውን እንመልከት።

*“ጃንሆይ በየጊዜው አዳሪ ት/ቤቶችን ከቀትር በኋላ ሲጎበኙ ብርቱካንና ሙዝ ያሳድላሉ። የአዲስ አበባ ተማሪዎች በሙሉ ለገና በአል ቤተመንግስት ሄደን ለእያንዳንዳችን ሹራብና ብስኩት ይሰጠናል። በአመት መጨረሻ ላይ ሁሉም በሰልፍ ወደ ቤተ መንግስት ሄዶ በየክፍሉ ጥሩ ውጤት ላመጡት ተማሪዎች ሽልማት ይሰጣል”* ይሉናል ።

ይህ የጃንሆይ ልዩ ባህሪ የንግስና ዘመናቸው ማብቂያ አካባቢ ድረስ የዘለቀ ነበር። የራሴን ገጠመኝ ላክል። ልጆች ሆነን ጃንሆይ በሚያልፉባቸው መንገዶች መምጣታቸውን አስቀድሞ የሚያሳውቀው ‘በቀለ ጢሞ’ የተባለ ዱቅዱቄ (ሞተር ብስክሌት) ነጂ ምልክት እያሰማ ከኦቶሞቦሎቹ ፊት ለፊት ሲነዳ ጃንሆን ከት/ቤት የሚወጡ ተማሪዎች ሲያገኙ ወይም ጉልት አካባቢ ሲደርሱ ኦቶሞቢሎቻቸው ይቆሙና ለተማሪው / ለህዝቡ ብር ያድሉ ነበር። ታዲያ በዚህ መንገድ በተለያዩ አጋጣሚዎች ከጃንሆይ ብር ከተቀበሉት መካከል አንዱ ነኝና የአቶ ፍቅሩ ትረካ እንዲህ ያሉ ትዝታዎችን አጭሮብኛል።

ከፒያሳ ልጅ ተዝቆ ከማያልቀው አስገራሚ ትረካዎች መካከል የሚከተለውን ደግሞ እንቅመስ። *“…አልፎ አልፎ ፀጉርን ካለመታጠብ የሚመጡ ተባዮችን በማስለቀም የጂሌት ምላጭ የሌለው በጠርሙስ ስባሪ እየላጨ ቁንጮ ይሰራል። ይህን ሁሉ ችግር በመረዳት ነው የትምህርትና ስነ ጥበብ ሚኒስቴር በየተማሪ ቤቱ ሰራተኛ እየላከ ዲዲቲ ጭንቅላታችን ላይ ሲያስረጭ የነበረው።…”* ይሉናል። ይህ የትምህርት ሚኒስቴር ተግባር እጅግ ያስደምመናል። እውነት ያ! ዘመን እንዲህ ነበርን? ብለን በውስጣችን እንድንገረም ያደርገናል። ምናልባትም በዚህ ዘመን ከምናሳልፈው ህይወት አንፃር ተነስተን ‘ምነው ቁንጮ ሁኜ ያኔ በኖርኩ?’ ያሰኘንም ይሆናል።

አቶ ፍቅሩ የገለፁልን የት/ሚኒስቴር ተግባር ትውስታቸው በዚህ ብቻ የሚያበቃ ሳይሆን ሌሎችንም ተግባራቱን በየምእራፎቹ ዘርዝረዋል። የዚያን ዘመን የሚኒስቴር መስሪያ ቤቶች የግልጋሎት አሰጣጣቸውን ስናነብ ዛሬ ባለንበት ዘመን ውስጥ በሀገራችን የሚገኙትን የሚኒስቴር መ/ቤቶች ስነ ግልጋሎትና የባለ ስልጣናቱንም ምግባርና የሞራል ብቃት እናነፃፅር ዘንዳ ግድ ይለናል።

የዚያን ዘመን መንግስታዊ መ/ቤቶች ሃላፊዎች በቅን ልቡና ሀገራቸውን የሚያገለግሉ ብቻ ሳይሆኑ የሰራተኛውን መብትም አክብረው የሚያስከብሩ ነበሩ። እነሆ አብነት፤

*“…ፍራንኮ ፎኑ አቶ አሃዱ ሳቡሬ ላገራችን ስፖርት እድገት የሚጥሩ ስለነበሩ ሙሉ ድጋፋቸውን ሰጥተውኝ፣ የዛሬይቱ ኢትዮጵያ ቋሚ የስፖርት አምድ ከፈተ። አንዳንዴ የመቻልና የመኩሪያን ቡድኖች ነካ ሳደርጋቸው ወዳጆቻቸው የሆኑ መኮንኖች፣ ’ምነው የዛሬይቱ ይህንን ፃፈ?’ ሲሉዋቸው ‘ትክክል ስለሆነ ነው’ በማለት የጋዜጠኛውን መብት ያስከብራሉ።…”* ሲሉ ያወጉናል አዛውንቱ ያራዳ ልጅ አቶ ፍቅሩ። ዛሬ ዘመንስ? ብለን እንጠይቅ።

ዛሬ ዘመንማ እንኳን እንደነ አቶ አሃዱ ሳቡሬ የመሳሰሉ የመብትና የነፃነት ተቆርቋሪዎች ኖረው የሰራተኛውን መብት አክብረው ሊያስከብሩ ይቅርና ራሳቸው የመብትና የነፃነት ገፋፊነታቸው በቀጠራቸው የህወሃት መንግስት ሰርተፊኬት የተረጋገጠላቸው ሲሆኑ ብቻ ነው የሚሾሙት። ዘመን አያሳየው የለ! አንድ አስገራሚ ስለዛ ዘመን ማጠናከሪያ ከፒያሳ ልጅ ልጨምርላችሁ።

*“ጣሊያን ኢትዮጵያን በወረረች ጊዜ ሜክሲኮ የኛ ደጋፊና ተከራካሪ ስለነበረች በአዲስ አበባ አንድ አደባባይ በስሟ ተሰይሟል።…በ1968 ሜክሲኮ የኦሎምፒክ ጨዋታዎችን ለማስተናገድ ስትዋትት፣ ኢንተርናሽናል ኦሎምፒክ ኮሚቴ በዘር ልዩነት ምክንያት ከኦሎምፒክ ጨዋታ የታገደችውን ደቡብ አፍሪካ እንድትጋበዝ ወሰነ። የኢትዮጵያ ኦሎምፒክ ኮሚቴ ደቡብ አፍሪካ ከተጋበዘች በጨዋታዎቹ የማይካፈል መሆኑን ለጋዜጠኞች መግለጫ ሰጠ። ከአባላቱ መካከል 41 አገሮች የኢትዮጵያን ሀሳብ በመደገፍ ደቡብ አፍሪካ ከተካፈለች የማይካፈሉ መሆናቸውን አሳወቁ። አዲስ አበባ የሚገኘው የሜክሲኮ አምባሳደር…አቤቱታውን ለውጭ ጉዳይ ሚኒስቴርና ለጠቅላይ ሚኒስቴር ፅ/ቤት አቀረቡ።…*

*“ጃንሆይ ፀሀፊ ትእዛዝ አክሊሉ ሃብተወልድንና አቶ ከተማ ይፍሩን (ጠቅላይ ሚኒሰትሩንና የውጪ ጉዳይ ሚኒስትሩን) ጠየቋቸው። እነሱም … ‘ምንም የምናውቀው ነገር የለም’ (ስለ ውሳኔው) በማለት መለሱ። ከጃንሆይ አካባቢ አንድ ሰው ይድነቃቸው ሊሆን ይችላል በማለት ጠቁሞ እንዲጠራ ተደረገ። ጃንሆይ፣ ‘አንተ ነህ ወይ ኢትዮጵያ አትካፈልም ብለህ የወሰንከው?’ ብለው ጋሼ ይድነቃቸውን ጠየቁት። ‘አዎን እኔ ነኝ ‘ በማለት መለሰላቸው። ‘አክሊሉንና ከተማን ሳታማክር እንዴት መግለጫ ትሰጣለህ’ ሲሉት፣ ‘ግርማዊነትዎ ዘረኛው የደቡብ አፍሪካ መንግስት በማንኛውም መድረክ እንዳትካፈል መታገል እንዳለብን ቋሚ ትእዛዝ ሰጥተዋል።…በተጨማሪም ጉዳዩ መንግስትን ስለማይመለከተው ውሳኔውን የሰጠው የኢትዮጵያ ኦሎምፒክ ኮሚቴ ነው’ ብሎ መለሰላቸው።*

**“ጃንሆይም ደስ ብሏቸው፣** *‘በል ለሜክሲኮ አምባሳደር ደውለህ አስረዳው’* በማለት ትእዛዝ ሰጡ።…”

አንባቢያን ሆይ! የኢትዮጵያ አምላክ ያሳያችሁ! የጋሼ ይድነቃቸው ውሳኔና ምላሽ ሲደንቀን የጃንሆይ መልስ ደግሞ መባሱ!! ለመሆኑ ኢትዮጵያችን በዛን ዘመን! እንዲህ ያሉ መሪ ነበራትን? ብላችሁ ውስጣችሁን ዘልቆ እስኪሰማችሁ ድረስ አልተገረማችሁም? የጃንሆይ ፍፃሜም በእዝነ ልቡናችሁ ከመቅፅበት ድቅን ብሎ አንጀታችሁ አልተላወሰባችሁም?

እርግጥ ነው በግርማዊነታቸው ***የአስተዳደር ዘመን*** ጥፋትና በደል አልተሰራም ማለት አይደለም። ጥፋትም ነበር፣ በደልም ደርሷል። ይሁንና ግርማዊነታቸውን ከተኳቸው ***ሁለት የአገዛዝ ዘመኖች*** አንፃር ግን ያ ዘመን ለኢትዮጵያ እድገት ባበረከተው ወይም ባጠፋው ጭብጥ አንፃር በፍፁም በምንም መልኩ  ከሁለቱ አገዛዞች ጋር በአንድ ሚዛን ሊለካ አይችልም።

ቀዳማዊው ማርሻል ጃፈርሶ (ኮሎኔል መንግስቱ ሃይለማርያም)ም ሆኑ ወይም እርሳቸውን የተኳቸው ዳግማዊው ማርሻል ጃፈርሶ (አቶ መለስ ዜናዊ) በአመራር ብቃትም ሆነ በሰብእና ጥንካሬና ሞራል፣ በአርቆ አሳቢነትም ሆነ በአለም መድረክ አስተዋፅዖ አበርካችነት አንዳቸውም ቢሆኑ ግርማዊነታቸውን ቅንጣት ታህል እንደማይደርሱባቸው ታሪክ ምስክር ሆኖላቸዋል። እድሜ ሰጥቶን እኛም በአይናችን እያየን እንገኛለን፣ ይህንን ታሪክ ለዘከሩልን አቶ ፍቅሩ ምስጋና ይግባቸውና።

ይህንን ንኡስ ርእስ ከመቋጨቴ በፊት ስለዛ! የየዋህነትና የቅንነት ዘመን ማሳረጊያ ይሆን ዘንዳ አንድ ጀባ ልበላችሁ፣ ከፒያሳ ልጅ። *“…በዚያን ዘመን ላውንደሪ ስላልነበረ እንደኛ አይነቱ ወንደላጤ ከሰፈር ልብስ ሰብስቦ በቀበና ወንዝ አጥቦ ተኩሶ ለሚያመጣ አጣቢ ይሰጣል። የሚገርመው አጣቢው የሰበሰበውን ልብስ ባለቤት ለይቶ ማወቁና በእሱም*

*ላይ የነበረን እምነት ነው። አጣቢ መሆኑ ይታወቅ እንጂ ሱቅና አድራሻ አልነበረውም።…"*
አጃኢብ ነው! አሁን ዘመንማ መተማመን ውሃ ጠጥታለች። ቅንነት ድራሽ አባቷ ጠፍቷል። ታማኝነት ካገር ወጥታለች። ህሊና ህሊናዋን አጥታለች። ይብላን ለእኛ…

## <u>የዛ ዘመን ትውልድ!</u>

ኢትዮጵ ሀገሬ ፤ ቅጥ አጥቷል ሀዘንሽ
ያቆሰለሽ ልጅሽ
የሞተልሽ ልጅሽ
ገዳዩም ካብራክሽ።

የፒያሳን ልጅ አንብቤ ስጨርስ በውስጡ የቀረቡት በርካታ የዛ ዘመን ትውልድ ኢ. ትዮጵያዊያን ታሪክና መጨረሻቸው ልቤን ቢነካውና ውስጤን ቢጠዘጥዘው የጫርኩት ስንኝ ነበር - ከላይ ያለው።

እርግጥ ነው ሞትና እስር፣ ስደትና እንግልት የትውልዱ መታወቂያ በሆነው በ1966 ዓ/ም አብዮት ወቅት ወጣት ሀይል (ከሃያው እድሜ በታች) ከነበረው አካል ብሆንምና ለአመታት በእስር መማቀቅን (በዘመነ ደርግ)፣ ቶርቸርንና እንግልትን በሚገባ ባውቃቸውም፣ ሞትንም ደጋግሜ ብራመደውምና እጣ ክፍሌ ስደት ቢሆንም፣ ዛሬ ላይ ሆኜ መለስ ብዬ ሳስበው የእኛ ትውልድ *(ዛሬ በሃምሳዎቹ የእድሜ ክልል የሚገኘው)* ሀገርን በመገንባትና ፍሬ ያለው ቁብ ሰርተን ለተተኪው ትውልድ በማስረከብ ረገድ የምንታወቅበት አኩሪ ሀውልት የለንም። (ልብ በሉ፣ ዳግማዊው ማርሻል ጃፈርሶ - አቶ መለስ ዜናዊ - እና 'በእንስሳት አብዮት' /አኒማል ፋርም/ መፅሀፍ ውስጥ የሚገኘውን የናፖሊዮን አፈቀላጤ ስኩለርን የሚወክለው በረከት ስምዖን እና አብዛኞቹ የህወሃት አመራሮችና ሳተላይቶቻቸው፣ እንዲሁም በተቃራኒው ጎራ ከሚገኙት ተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶች መሪዎች አብዛኞቹ ዛሬ በሃምሳዎቹ የእድሜ ክልል ውስጥ የሚገኙ ናቸው።) ይልቁንም ከ1966 አብዮት ወዲህ እርስ በርሳችን እየተላለቅን፣ እርስ በርሳችን እየተጠላለፍን፣ ለአጥፊዎች ተመችተን፣ ሀገራችንና ህዝባችን የነበራቸውን አጥተው ከድጡ ወደ ማጡ የሆነ የጨለማ ጉዞ ከጀመርን አርባኛውን አመት ልንጨልጥ እንጥፍጣፊው ቀርቶናል። …ለማንኛውም የእኛን በዚህ ገትቼ የዛ! ዘመን ትውልድን ተምሳሌያዊ የታሪክ ምግባራት ከፒያሳ ልጅ ውስጥ ቀነጣጥቤ በሚከተለው ብንጀምርስ?

*"በኮተቤ የቀዳማዊ ሃይለ ስላሴ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ከተከፈተ በኋላ ዳግማዊ ምኒልክ፣ ተፈሪ መኮንን፣ መድሃኔ አለም፣ ጀኔራል ዊንጌት፣ ጎንደይራድ ተግባረ እድ፣ ተጠናከሩ። በመቀጠል ዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ፣ ዓለማያ ኮሌጅና ህንፃ ኮሌጅ ተቋቁመው ትምህርት ተስፋፋ። ትምህርታቸውን የፈፀሙት ሁሉ በብዛት በትምህርት ሚኒስቴር አማካይነት ወደ አውሮፓ አሜሪካ፣ ካናዳ፣ አውስትራሊያ ጭምር ተልከው በልዩ ልዩ ሙያ ሰልጥነው በመመለስ ሀገራቸውን አገልግለዋል።…"*

ይህ የሆነው እንግዲህ በዛ ዘመን ነበር። ከዛ ወዲህስ? ብለን እንጠይቅ። ከዛ ወዲህማ በእኛ ዘመን አጋጣሚ አግኝቶ ለትምህርትም ሆነ ለሴሚናር ወይም ለስፖርት ውድድር ከሀገሩ ከወጣ ወደ ሀገሩ የሚመለስ አለመኖሩ በዛ ዘመንና በዚህ ዘመን መካከል ያለውን ገደል ክፍተት ያመለክታል። ይህ ለምን ሆነ? እስከመቼስ ሀገራችን 'ብሩህ አእምሮዎቿን' ስትራቆት ትኖራለች? ለሚለው ግን ምላሹ የእያንዳንዱ አንባቢ ይሆናል።

እንቀጥል።

*"ግርማዊ ቀዳማዊ ሃይለ ሥላሴ አልጋ ወራሽ በነበሩበት ወቅት በ1924 በፈረንሳይ ሀገር በፓሪ ከተማ የተዘጋጀውን የኦሎምፒክ ጨዋታዎችን በእንግድነት ተገኝተው ስላዩ በ1928 በአምስተርዳም (ሆላንድ) በሚደረገው ጨዋታ እንድትካፈል ጥረት አድርገዋል።...ስፖርት ሀገራችን ውስጥ እንዲስፋፋ ፍላጎት ስለነበራቸው በ1948 የመጀመሪያው የኢትዮጵያ ስፖርት ኮንፌዴሬሽን እንዲቋቋም፣ የኢትዮጵያ ኦሎምፒክ ኮሚቴ እንዲመሰረትና አትሌቶቻችን በኦሎምፒክ ጨዋታ እንዲካፈሉ በነጋሪት ጋዜጣ አወጁ።"*

እነሆ ጃንሆይ በህግ እንዲቋቋሙ ያደረጓቸው የኢትዮጵያ ስፖርት ተቋማት እነ አቶ ይድነቃቸው ተሰማን፣ አቶ ፍቅሩ ኪዳኔን እና በፒያሳ ልጅ ውስጥ ስማቸው የተዘረዘሩ ምርጥ ዓለም አቀፍ የስፖርት አደራጆችን፣ መሪዎችንና ምሁራንን አፍርቷል።

ለዛሬዎቹ ስመጥር አትሌቶቻችን ራዕይና የድል መሰረቱ በዚያ ዘመን የተጣለው ተቋም ነው። እነ አበበ ቢቂላና ማሞ ወልዴም ኢትዮጵያን በዓለም የስፖርት መድረክ ሰንደቋን ከፍ አድርገው በማውለብለብ ፋና ወጊ የሆኑ የዛ ዘመን ትውልድ አካል ናቸው።

ስለስፖርት ኮንፌዴሬሽኑ የመጀመሪያ ፕሬዚዳንት ብርጋዴር ጄኔራል አብይ አበበ አቶ ፍቅሩ ሲፅፉ፣ *"...ትሁት፣ ሰላምተኛ፣ ሁሉን በእኩል የሚያዩ ከፍተኛ ባለስልጣን ጄኔራል አብይ አበበ ህይወታቸው በግፍ እስካለፈበት ድረስ የኢትዮጵያ የስፖርት እድገትን ደግፈዋል።"* ይላሉ፣ በፀፀት ድባብ። ይህንን የመሳሰሉ አያሌ ሌሎች ታሪኮችን ለመፅሀፉ አንባቢያን ትቼ ወደ ሌላ ነጥብ ላምራ።

*"...ፓትሪስ ሉሙምባን (የመጀመሪያው የኮንጎ ጠ/ሚኒስትር) ከሊዎፓልዳቪል (አሁን ኪንሻሳ) ወደ ስታንሊይቪል ያመጣው ዲሲ ስሪ አውሮፕላን ኢትዮጵያ ለተባበሩት መንግስታት ያዋሰችው ሲሆን አብራሪው የመቶ አለቃ ፋንታ በላይ (ሜጀር ጄኔራል ሆኖ ደርግ በግፍ የገደለው) ነበር። ሉሙምባ የጥቁር አብራሪዎችንና (በ1960 እኤአ) ቴክኒሺያን ሲያዩ ለመጀመሪያ ጊዜ መሆኑንና ኢትዮጵያ አፍሪካን የምታኮራ ሀገር መሆኗን ተናግረዋል።"*

እርግጥ ነው የዛን ዘመኗ ኢትዮጵያ በዓለም አቀፍ መድረክ የተከበረች፣ ተሰሚና የ አቅሟን ያህልም ሌሎችን ከመርዳት ወደ ኋላ የማትል የአኩሪ ትውልድ ውጤት ሆና ነበር፣ ይህ ሁሉ ከመቀልበሱ በፊት። በድፍን አፍሪካ አልፎም እስከ ካሬቢያን ድረስ፣ ራሷን በራሷ የምታስተዳድር ነፃ ሀገር በመሆኗ፣ ብዙዎች የሚመኩባትና በአርአያነት የሚመለከቷትም ሀገር ነበረች።

ራሳቸው የኮኖን ዘማች የነበሩት አቶ ፍቅሩ፣ በኮኖን ለዘመተው የተባበሩት መንግስታት የጦር ሃይል ኢታማጆር ሹም ሆነው ያገለገሉት ኢትዮጵያዊው ጄኔራል ኢያሱ መኮንን መሆናቸውን ያጫውቱናል።

ዛሬ እንዲህ ያለውን ታላቅ ሹመት የሚወስዱት የአሜሪካንና የአውሮፓ ጄኔራሎች ናቸው። የዛ! ትውልድ የጦር ሃይሎቻችን መኮንኖች የነበሩት በታወቁ የኤሮፓና የአሜሪካ የጦር አካዳሚዎች ውስጥ ከፍተኛ ወታደራዊ ሳይንስ የተማሩና የተመረቁ እንጂ ማእረጋቸውና ሙያዊ ብቃታቸው እንዲህ እንደ ዛሬው በዘር መስፈርት ተለክቶ ከጫካ የተገኘ ወፍ ዘራሽ ማእረግ አልነበረም።

ይህን በዚሁ ገትተን የሚከተለውን አስደማሚ ታሪክ ደግሞ እንመልከት።

*"...በኮንን በደረሰው ድርቅ ምክንያት ኢትዮጵያ በአስራ አንድ ዲሲ ስሪ አውሮፕላን ጉዞ ተሳፍሮ የላከችውን የምግብ እርዳታ በኢትዮጵያ ጦር አማካይነት እንዲታደል ታዞ በካፒቴን ንጉሴ ደምሰሴ አብራሪነት በአውሮፕላን እየዞርን (ኮኖን ውስጥ) የማከፋፍለው እኔ (አቶ ፍቅሩ) ነበርኩ።... ጥንትማ እንኳን ለኮንን ይቅርና አደጋ ለደረሰባቸው የአውሮፓ ሀገሮች ያቅማችንን ያህል የገንዘብ እርዳታ ልከናል።"*

ይህንን ስናነብ ወደድንም ጠላንም ዛሬስ? የሚለው ጥያቄ ህሊናችን ውስጥ ደጋግሞ መደወሉ አይቀሬ ነው። ለ1966 ዓ/ም አብዮት መነሻ አስተዋፅዖ ያደረገው በተፈጥሮ አየር መዛባት የደረሰብን ድርቅና ለድርቁም የተሰጠው አሰተዳደራዊ ምላሽ ነበር። እነሆ ያ! ጊዜ አሁን አራት አስርታትን አልፏል። ይሁንና በነዚህ ረጅም አርባ አመታት ውስጥ በረሀብ ሳቢያ የሚያልቀውን ህዝባችንን ከረሀብና ከድርቅ ለመታደግ ምን ተደርጓል? በአጭሩ ምንም!

የሀገራችን ገገርዎች ዛሬም የልመና አቁማዳቸውን ይዘው በአለም ዙሪያ ርጥባን ሲጠይቁ አንዳችም ሀፍረት የማይሰማቸውና ኢትዮጵያዊ ኩራታቸውን ገፍፈው የጣሉ በመሆናቸው ዛሬ አብዛኛው የዓለም ማህበረሰብ ኢትዮጵያ ማለት ትርጉሙ ረሀብ ማለት የሚመስላቸው በመሆኑ በስደት አለም ያለነው ኢትዮጵያዊያን የቀን ተቀን ገጠመኛችንና የማንነት ሰቀቃችን ሆኖ ይገኛል።

በያዝነው ግንቦት ወር ሃያኛውን የአገዛዝ ዘመኑን የሚጨርሰው የህወሃት ገገርዎች ለተራበ ህዝብ ደንታ የሌላቸው ኢሰብአዊያን ለመሆናቸው ከጫካው ዘመን ታሪካቸው ጀምሮ በተግባር ያስመሰከሩትና አሁንም በማስመስከር ላይ ያሉ ለመሆናቸው የእርዳታ ስንዴ ሸጠው ቦንብ በመግዛት የረሀብተኛውን አስትፋስ ዘግተው አፅሙን ለጥንብ አንሳ አሳልፈው መስጠታቸው ብቻውን በቂ የታሪክ ማስረጃ ነው። ህወሃትን የሚያስጨንቀው ኢትዮጵያን ምርታማ አድርጎ ረሀብን ማጥፋቱ ሳይሆን እንደምን አድርጎ አገዛዙን ከዘንድሮ ወደ ከርሞ እንደሚያሸጋግረው እኒ፟! "የተራበ ህዝብ ለስንዴ ራሽን እንጂ ለፖለቲካ 'አፐታይት' የለውም" የሚለው ያልተፃፈው የህወሃት መሪዎች መመሪያ በተደጋጋሚ በህዝባችን ላይ የሚደርሰውን የረሀብ ቸነፈር ለፖለቲካ እድሜ ማራዘሚያ እየተጠቀሙበት ይገኛሉ።

ለማንኛውም ታሪክን ለታሪክ ተንታኞች አቀይተን፤ ተዝቆ ከማያልቀው የፒያሳ ልጅ ትተራ የሚከተለውን ደግሞ እንዝገን።

*"...ናሚቢያ በደቡብ አፍሪካ /አፓርታይዳዊ አገዛዝ በነበረበት ዘመን/ ቁጥጥር ስር እንዳትሆን ኢትዮጵያ ከላይቤሪያ ጋር ጠበቃ በመቅጠር በሄግ ከተማ ሆላንድ ውስጥ በሚገኘው ኢንተርናሽናል ፍርድ ቤት ተከራክራለች።"*

ይህ እንዲሆን ያደረጉት ጃንሆይ በቀዳማዊው ማርሻል ጃፈርሶ (ኮሎኔል መንግስቱ ሃይለማርያም) በግፍ ሲገደሉ፤ ዳግማዊው ማርሻል ጃፈርሶ (አቶ መለስ ዜናዊ) በበኩላቸው የግርማዊነታቸው አፅም በሚያከብሯቸው የአለም መሪዎች (ለምሳሌ በቀብሩ ላይ ለመገኘት ጠየቀው እንደተከለከሉት ኔልሰን ማንደላ) በክብር ታጅቦ ስንብት እንዳይደረግለት ማገዳቸው የሁለቱ ማርሻል ጃፈርሶዎችን አንድነት ቁልጭ አድርጎ ያሳያል። በግርማዊነታቸው ዘመነ አስተዳደር የተደረገው ታላቅ ተግባር ግን የሀገራችንና የህዝባችን የዘላለም ቅርስ ነው።

እንቀጥል ዳሰሳችንን።

*"ማንዴላ ከመታሰራቸው በፊት ትግላቸውን ለአፍሪካ ህዝብ ለማስረዳት ባከናወኑት ጉዞ መጀመሪያ የመጡት ወደ ኢትዮጵያ መሆኑ ይታወሳል። ያኔም በጃንሆይ መልካም ፈቃድ የኢትዮጵያ ዲፕሎማቲክ ፓስፖርትና ለሆቴል ወጪ የሚሆን ገንዘብ ተሰጥቷቸው የ አፍሪካን ነፃ ሀገሮች ጎብኝተው ወደ አዲስ አበባ ከተመለሱ በኋላ በኮልፌ ወታደራዊ ውጊያ ስልጠና ወስደዋል።..."*

ይህን የፒያሳ ልጅ ታሪክ ማንዴላ ከእስር ከተፈቱ በኋላ ተናግረውታልም፣ ፅፈውታልም። 'ሎንግ ዎክ ቱ ፍሪደም' በተባለው መፅሀፋቸው ውስጥ ማንዴላ ለኢትዮጵያ ልዩ ክብርና ፍቅር እንዳለቸው በአፅንዖት አስቀምጠዋል።

እንሻገር ወደ ሌላ።

*"...በ1957 ጋና ነፃ እንደ ወጣች፣ ፕሬዙዳንት ንክሩማ በመጀመሪያ የጎበኙት ሀገር ኢትዮጵያ መሆኑን አስታውሳለሁ።... የአፍሪካ ሀገሮች ለነፃነታቸው በታገሉበት ወቅት የ ኢትዮጵያ መንግስት የሚቻለውን ያህል በውጪ ጉዳይ ሚኒስትር አማካይነት ለሁሉም እርዳታ አበርክቷል። ብዙዎች ግን ረስተውታል። በስልጣን ላይ ያለውን መንግስት ላለማስቀየም ብለው ይሆናል በጃንሆይ ጊዜ የተደረገውን የሚጠቅስ የለም።... የኢትዮጵያ ነፃነት፣ ታሪክና ባህል ለብዙዎች አፍሪካዊያን አይዋጥላቸውም። ... እኛም ብንሆን ሀገራችን የፈፀመችውን አኩሪ ስራዎች በደንብ ለማስረዳት ባለመቻላችን ወይም ባለመፈለጋችን በሌሎች ላይ መፍረድ ያዳግታል። የማስታወቂያ ሚኒስትሩም የወቅቱን ፕሮፓጋንዳ ከመርጨትና ከዚያ በፊት ምንም እንዳልተሰራ ለማስረዳት ከመሞከር በቀር ታሪክን ማውሳት አይፈልጉም።..."*

አዎ፣ እውነት ፅፈዋል አቶ ፍቅሩ! በተለይ ባለፉት ሃያ አመታት በህወሃት አገዛዝ ሆን ተብሎ በስፋትና በግልፅ ሲለፋና ሲደከምበት የቆየውና ዛሬም ያላባራው መሰረታዊ ግብ የ ኢትዮጵያን ታሪክና ግዛት እንዳልነበረ አድርጎ መናድ ነው።

ከቅኝ ግዛት አገዛዝ ነፃ የወጣችው ጋና ደስታዋን መጀመሪያ የተጋራቸው ከኢትዮጵያ ጋር ነበር፣ ምክንያቱም ኢትዮጵያ የነፃነት ተምሳሌ ነበረችና! ጥቁር አሜሪካዊው ፕሬዚዳንት ባራክ ኦባማ የመጀመሪያ የአፍሪካ ጉብኝታቸውን ያደረጉት በነፃነት ቀንዲሏ ኢትዮጵያ ሳይሆን በጋና ነበር። ለምን?

ምክንያቱም የዛሬይቷ ኢትዮጵያ የምትታወቀው እንደ ቀድሞዋ በነፃነት ተምሳሌነቷ ሳይሆን በግፍ አገዛዝ፣ በድህነትና በረቀቀ የጎሳ ፖለቲካ አራማጅነቷ በመሆኑ ነው!!

ዳግማዊው ማርሻል ጃፈርሶ አቶ መለስ ዜናዊና አጫፋሪዎቻቸው የአፍሪካ መንግስታት መሪዎችን አዲስ አበባ ላይ ሲቀበሉ ደረታቸውን አሳብጠው የሚንጎማለሉበት የአፍሪካ አንድነት ድርጅት ፅ/ቤት ኢትዮጵያ መዲና ላይ እንዲተከል ያደረጉት ጃንሆይና የዛ! ዘመን የኢትዮጵያ መሪዎች ናቸው! የዛ ዘመን! ትውልድ የታሪክ ሀውልት።

ለማንኛውም የዛ! ዘመን ትውልድ! የሚለውን ንኡስ ርእስ በሚከተለው የአቶ ፍቅሩ ሀዘናዊ ትዝብት ብንቋጨውስ?

*"...በጣም የሚያሳዝነኝ ባስተሳሰቡና በእውቀቱ፣ በህግ አርቃቂነቱ፣ የአፍሪካን መብት ባስከባሪነቱ በዓለም ደረጃ የታወቀው...አቶ ይድነቃቸው ተሰማ ላገሩ ምንም እንዳልሰራ ሰው መረሳቱ መታሰቢያ እንኳን ማጣቱ ነው።... ጋሼ ይድነቃቸው ብቻ ሳይሆን ብዙ አዛውንቶች ጀብዱና ከፍተኛ ድርጊት የፈፀሙ በመፈንቅለ መንግስት በግፍ የተፈጁት*

*ጭምር ላገራቸው ያበረከቱት አስተዋፅዖ መረሳት አልነበረበትም። ህዝቡም አዲሱም ትውልድ ስለእነሱ ማወቅ አለበት።...ጀግንሆይንም፣ አዛውንቶቻችንንና ላገራቸው የደከሙትን፣ የታገሉትን ባንረሳቸው ጥሩ ነው።...ለማውቃቸውም ሆነ ለማላውቃቸው፣ ሀገራችንን ላቀኑት፣ ለነፃነቷ ለታገሉት ሁሉ አክብሮቴ ምን ጊዜም ይቀጥላል።...*

*"ሀገራችን ምንም ድሃ ብትሆን በተቻላት መጠን ሁሉም ትምህርት ገብይቶ እንዲያገለግላት ጥራለች።...መተቸት ቀላል ስለሆነ 'ይህ ቢሆን ኖሮ' የሚልም አይጠፋም። መረሳት የሌለበት አሁን የምንጠቀምባቸውና የምንገለገልባቸው ሁሉ መሰረት የተጣለበት በኛ ዘመን መሆኑን ነው። እኔ ተወልጄ ያደግሁት፣ በስራም ላይ የዋልኩት፣ በሀገሬ የኖርኩት በንጉሡ ነገሥቱ ዘመነ መንግስት ነው። በዚያ ጊዜ ኢትዮጵያ በዓለም ተከብራ፣ እኛም ኮርተንባት፣ ሁሉም ዘር ተቀላቅሎ በአንድነትና በሰላም ይኖር ነበር።..."*

## ማሳረጊያ

አቶ ፍቅሩ ኪዳኔ፣ የአራዳው አዛውንት፣ በቱሪስትነት ሳይሆን በስራ ጉዳይ በዓለም ዙሪያ በአንድ መቶ ሰማኒያ ስምንት ሀገራት ውስጥ ተዘዋውረው ሰርተዋል። ከአፍሪካ በሃምሳ ሶስት፣ ከአውሮፓ በአስራ ዘጠኝ፣ ከአሜሪካ በሰላሳ ዘጠኝ፣ ከእስያ በሰላሳ ስድስት፣ ከ ኦሺያና (የዚህ ቅኝት አቅራቢ የሚኖርባትን አውስትራሊያን ጨምሮ) በአስራ አንድ ሀገራት ተዘዋውረው አገልግለዋል። ዛሬም ዓልም አቀፋዊ ስራዎቻቸውን አላቋረጡም።

በእኒህ ሀገራት ውስጥ ከሚገኙ ፕሬዚዳንቶች፣ ጠ/ሚኒስትሮች፣ ወታደራዊ አገዛዝ መሪዎች፣ ነገስታት፣ ልዕልታት፣ ሼሆች፣ ሚሊየነሮች፣ እውቅ ግለሰቦች ወዘተ ጋር በአንድ ጠረጴዛ ዙሪያ ተቀምጠዋል። ማእድ ተካፍለዋል። እጅ ለእጅ ተጨባብጠዋል። ለሰአታት አውግተዋል።

ታዲያ ይህንን ስታነቡ 'እኒህ ሰው ዲፕሎማት ነበሩ እንዴ?' የምትሉ አትጠፉም። ከእኔ ይልቅ መልሱን ለምን በራሳቸው አንደበት አያወጓችሁም? እናም ጥልቅ ለሆነው ለአቶ ፍቅሩ ኪዳኔ የታሪክ ወግ እነሆ የፒያሳን ልጅ ታነቡት ዘንዳ ጋብዣችኋለሁ።

ያልተቃጠለው ቤተ መፃህፍት - አቶ ፍቅሩ ኪዳኔ - በፒያሳ ልጅ የዳሰሷቸው የካታሎግ ዘሮች ብዙ ናቸው። ለምሳሌ ከኔልሰን ማንዴላ ጋር በተደጋጋሚ ለረዥም ጊዜ ተገናኝተው መወያየታቸውን ገልፀውልናል። አያይዘውም ይህ ራሱን የቻለ መፅሀፍ እንደሚወጣው ጠቁመዋል። ይህ እንግዲህ ከቤተ መፃህፍቱ ካታሎጎች አንዱ ሲሆን ታሪኩ በእጃችን ገብቶ እናነበው ዘንዳ እንፀልያለን። የጋሼ ይድነቃቸው ዝርዝር ታሪክ ሌላው ነው። ይህንን ታሪክ ደግሞ ከአቶ ፍቅሩ በላይ አፍታቶ ለትውልድ ቅርስነት የሚያስረክብ ላይኖር ይችላልና ይህም በጥራዝ ሆኖ እናነበው ዘንዳ ሰላምና ጤና ለአቶ ፍቅሩ አይጓደሉባቸው ዘንድ እንፀልያለን። ለሌሎች ውጥን ስራዎቻቸው የቀን ብርሃን ማየትም ደግመን እንፀልያለን። አሜን!

በበኩሌ የፒያሳን ልጅ ላስነበቡኝ አቶ ፍቅሩ ኪዳኔ ልባዊ ምስጋናዬ ካሉበት ይድረሳቸው።

በያለንበት ቸር ይግጠመን!
መስፍን ማሞ ተሰማ
ግንቦት 2003 ዓ/ም
ሲዲኒ አውስትራሊያ

ለሚኖርዎት አስተያየት የኢሜል አድራሻዬ ይኸውሎ፣ msfntessema@yahoo.com.au